እስከ ፍጻሜው ድረስ ያለምንም ችግር በመጠናቀቁ በመስተዳድሩ ላይ የነበረን ጥርጣሬ ስህተት እንደነበር አረጋግጦልናል።

የሃዋሳ መስተዳድር በህጋዊና ትክክለኛ አሠራሩ ከልብ ሊመሰገንና ሊደነቅ የሚገባ ሲሆን፣ከዚህ ዓይነቱ አሰራርም ሌሎች ክልሎችና በተለይም የአዲስ አበባ መስተዳድር ሊማር ይገባል። የአዲስ አበባ መስተዳድር በአሁኑ ወቅት "የሠላማዊ ሰልፍና የህዝባዊ ስብሰባ ፈቃድ ክፍል" የሚል ህገ-መንግስታዊ ያልሆነ የራሱ መዋቅር ፈጥሮና "የሠላማዊ ሰልፍና የህዝባዊ ስብሰባ ፈቃድ ክፍል ኃላፊ" የሚል ባለስልጣን ሹሞ በዜጎች ህገ-መንግስታዊ መብት ላይ ፈቃጅና ከልካይ ሆኖ መገኘቱ ህገ-ወጥ አሰራር በመሆኑ ከሃዋሳ ከተማ መስተዳድር መማርና ስህተቱን ማረም ይገባዋል ብሎ ኢዴፓ ያምናል።

ኢዴፓ የወደፊቱ ፓርቲ!!

የኢዴፓ ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ

ሰኔ 3 ቀን 2001ዓ.ም

አዲስ አበባ